Amharic | አማርኛ



# የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመጀመር ዝግጁ ነዎት?

አሁን ልጅዎ 5 ዓመት ሆኖታል፣ ስለሆነም በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስለመመዝገብ ለማሰብ ጊዜው አሁን ነው።

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጀመሪያ ዓመት ፋውንዴሽን (ፕሬፕ/መሰናዶ) ይባላል። ልጆች ትምህርት በጀመሩበት አመት እስከ ኤፕሪል 30 ድረስ 5 አመት ከሞላቸው ፋውንዴሽን መጀመር ይችላሉ።

ዕድሜያቸው 6 ዓመት ለሆኑ ሕፃናት ትምህርት ቤት መግባት ግዴታ ነው።

## በቪክቶሪያ መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት እንዴት መመዝገብ እንደሚቻል

### ከማመልከትዎ በፊት

- ልጅዎ በእድሜው መሰረት በየትኛው አመት ትምህርት እንደሚጀምር ይወቁ
- ትምህርት ቤቶችን እና የትምህርት ቤትዎን ዞን በ **findmyschool.vic.gov.au** ያግኙ
- ትምህርት ቤቱን የሚጎበኙበት ጊዜ ለማስያዝ (ይሄ አማራጭ ነው) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ከተርም 1 ጀምሮ ያነጋግሩ።

### እንዴት ማመልከት እንደሚቻል

- የፋውንዴሽን (ፕሬፕ/መሰናዶ) ማመልከቻዎች ከተርም 2 መጀመሪያ ጀምሮ ይከፈታሉ
- የማመልከቻ ቅጽዎን በጁላይ ወር በመጨረሻው አርብ ያስገቡ
- ትምህርት ቤቱ በኦገስት የመጀመሪያዎቹ 2 ሳምንታት ውስጥ የማመልከቻ ውጤቱን በመያዝ ያነጋግርዎታል።

ተጨማሪ ለመረዳት
**vic.gov.au/enrolling-foundation-prep** ይመልከቱ

The Education State

VICTORIA State Government | Department of Education